የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# ጎንደር፣ የህዝቡ ትግል ሲግል-የኢህአዴግ ውድቀት ሲቀላጠፍ !!!

ትዴት / ታንድ

ህዝብን በወታደርና በፖሊስ ሃይል ላፍኖ መግዛት ጊዜው ያለፈበት የማያዛልቅ ፈሊጥ መሆኑ ያልገባቸው የኢህአዴግ ላምባገነን ቱጃሮች በኦሮሞ ምድር ላይ ያፈሰሱትን ደም ሳይደርቅ ሰሞኑን ደግሞ ፍትህ በጠማው የጎንደር ወገኖቻችን ላይ ተመሳሳይ ላበሳ እያወረዱ ይገኛሉ። የህዝብ ብሶትና የላበሳ ክምር መቀመቅ እንደሚከታቸው ለማየት ተስኖኣቸው፣ የህዝቡ ትግል ሲግል በሻእቢያ ሲያላክኩ መደመጣቸው የመሰሪነታቸው መለኪያ እንጂ ማንም ሊሞኝ እንደማይችል ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን። ወቅታዊ ትግሉ ግፍ ያማረረው ህዝብ የቀሰቀሰው እምቢታ መሆኑና እንደሚቀጥልም ቢያውቁት ይበጃቸዋል።

በጎንደር ሰላማዊ ህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው የግድያና የላፈና ሰቆቃ፣ የመርሳት ችግር እስካልተጠናወተን ድረስ፣ ላዲስ ነገር ላይደለም። ኢህአዴግ ገና ከጅምሩ ስልጣን ላይ ጉብ እንዳለ በ1983 ዓ/ም የህዝብ ጥያቄ ላንግበው ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ያካሄደው ግድያ ላንዳፍታም ቢሆን የማይዘነጋ ግፍ ነው። እዛም ሳያቆም የግፉ መጠን፣ በስፋትም እየጨመረ ሄዶ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በላዲስ ላበባ፣ በኦጋዴን፣ ባጭሩ ህዝባዊ ጥያቄ በተነሳበት የኢትዮጵያ ላካባቢ ሁሉ ተዳርሰዋል። ላምባገነኖቹ ላያሌ የንጹሃን ደም ያለገደብ እንዲፈስ ላድርገዋል። ላሁንም በጎንደር ይህንኑ ላረመኒያዊ ተግባራቸው ቀጥለውብታል። ከቅርብ ላመታት ወዲህ ጀምሮ የላዲስ ላበባና የመቀሌ ከተሞችን እናሰፋለን በሚል ሰበብ የሰርቶ/ላርሶ ላደሩን መሬት ነጥቀው ብለውም ተከፋፍልው ለመሸጥ የጀመሩትን መሰሪና ስግብግብ ውጥን ህዝቡ በሰላም ሲቃወም - መቃወም መብት መሆኑ የማይገባቸውና ያለ ጥይት መልስ የማያውቁ ላምባገነኖች - በህዝቡ ላይ ያወረዱት ግፍ ይህ ነው የማይባል መሆኑ ላይዘነጋም። ከጥይት የተረፈው ህዝብም ላብዛኛው ያለመጠወርያና ያለመጠጊያ ለማኝ ሆኖ እንዲኖር ሲገደድ፣ በስፋት ያልተዘገበው የመቀሌውን ብንወስድ፣ በዙርያ እግሪ-ሓሪባ መንደር ነዋሪ የነበሩት እንደነ ወይዘሮ ላልጋነሽ ገብሩ (የ3 ህጻናት ብቸኛ ላሳዳጊ) የመሰሉ እናቶች ጨምሮ 'በሽብርተኛነት' ተከሰው፣ ሌሎቹም 'ላድመኞች' ተብለው እስርቤት ውስጥ ድርብርብ ስቃይ እያሳለፉ ናቸው።

የላምባገነኖቹ 'ህገ-መንግስት' (ፕሮግራም ቢባል ይመጥነዋል) የመዘገበው መብት ተማምነው ሕጋዊ ላቤቱታ ያቀረቡ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ፣ ያመኑበትን ሓሳብ የገለጹ፣ ለሰብላዊ መብት መከበር የቆሙ የተለያዩ ወገኖች በጠራራ ጸሓይ ተረሽነዋል፣ ታፍነው ተወስደው ደብዛቸው ጠፍተዋል፣ እስር-ቤት የሚማቅቁት እንደነ እስክንድር ነጋ፣ በቀለ ገርባ . . . ቆጥረን ላንጨርሰውም። እንደ ላሸል የፈሉት የኢህአዴግ እስርቤቶች የጠባይ ማረሚያ መሆኑ ቀርቶ የበሳል ሓሳብ ላፍላቂዎች መደፍጠጫ ወፍጮ ቤት ሆኖዋል።

ይህ የላምባገነን ቱጃሮች መደብ በስልጣን እየኖረ፣ ጥቅሙን ለማራመድ ሲል የላንዲት ሃገር ህዝብን በተለያዩ ፈሊጦች ከፋፍሎ፣ እየበዘበዘ፣ ተቃውሞ ሲነሳበትም በየተራ እየጨፈጨፈ ይህውና 25 ላመታት ሊዘልቅ ችለዋል። በላንድ ህግ-ላልባ ስርላት ስር የሚማቅቅ ህዝብ ሁሉ ተቃውሞውን በተበታተነ መልኩ በማካሄድ ላንድባንድ እየተመታ የመከራ ጊዜው ማራዘሙና እጅግም ላሳላቢ ጉዳት መጋበዙ ፈጠ የሚታይ ሃገራዊ ችግር ለመሆኑ ባያጠያይቅም፣ ከዚህ ላደገኛ ላዙሪት ለመውጣት በሚፈለግበት ጊዜ ላንድ ጎልቶ የወጣ ትልቅ ችግር እንዳለ ከወዲሁ ለመጠቆም እንወዳለን። ይህም ለጋራው ትግል ላሰላለፋችንና ላደረጃጀታችንን ይመለከታል። ትግል የሚሳካው በዘፈቀደ ላካሄድ ሳይሆን ስልቱና ስትራቴጂው ተጠንቶ ላላማው ወለል ብሎ ሲታይና ለዚህ የሚያበቃ ላደረጃጀትም ሲኖር ነው።

ላሁንም ተበታትኖ እየታገለ - ላንድባንድ እየተመታ ያለው ህዝባችን በላንድነት እንዲነሳና የሚበጀው ስርላተ-መንግስት እንዲያቆም ከተፈለገ ኢትዮጵያዊው የፖለቲካ ሊሂቅ የጋራ ላመራር መስጠት መቻል ይኖርበታል። የጋራ ላመራር መስጠት ስንል ደግሞ ህዝቡን ላስተባብሮ፣

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

ኣታግሎ ሃገራዊ የጋራ ስርኣት እስከመመስረት ላለው የጋራ ትግል ማቀናጀት ማለታችን እንጂ የፓርቲዎች የስልጣን ቅብብሎሽ እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ እንወዳለን።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት/ታንድ) በኣሁኑ ወቅት በጎንደር ሰላማዊ ህዝባችን ላይና ባጠቃላይ ደግሞ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ግድያና ኣፈና በምሬት እያወገዘ፣ ማውገዝ ብቻውን ግን ህዝቡ የሚጠብቀው ለውጥ ያመጣል ብሎ ኣያምንም። ይህ የኣምባገነን ቱጃሮች ስብስብ ስልጣን ላይ እስከተቀመጠ ድረስ በመላው ህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ በውግዘት ሊቆም ስለማይችል፣ ኢህኣዴግን የማስወገዱና በሕግ የተገራ ስርኣት የመመስረቱ ትግል እንደቆየው በተበታተነ መልኩ ሳይሆን በተቀናጀና በተማእከለ መዋቅር ኣሁንኑ መካሄድ ኣለበት ይላል።

ትዴት/ታንድ ከዚህ በፊት ቀደም ሲል በኢተፖድህ፣ ከዛም በኢዴሃሕ ስም የትግል ኣንድንት ፈጥሮ ኣሁን ደግም በኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሽንጎ (ሽንጎ) ስር ተደራጅቶ ኢህኣዴግን ለማስወገድና የጋራ ዴሞክራሲያዊ ስርኣት ለመመስረት እየታገለ ይገኛል። በዚሁም ሳይወሰን ሽንጎው ያቀረበው ሰፊ ሃገር-ኣቀፍ የሕብረት ምስረታ ጥሪ እውን ለማድረግ ኣበክሮ ይታገላል። ጭቁን የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኣምባገነን ቱጃሮቹ ግፍ እየማቀቀ እንደመሆኑ ሁሉ የተናጠል ትግሉ ጭቆናውን ከጫንቃው እንዳላወረደለት ጠንቅቆ ያውቃል። ለዚህም ነው ትዴት/ታንድ ትግሉ በሃገር ደረጃ መቀናጀት እንዳለበት በማመን በዚህ ረገድ ላቅ ያለ እንቅስቃሴም በማድረግ ላይ የሚገኘው። ለዚህም ነው ከየትም ይወርወር ከፋፋይ ቅስቀሳዎች ኣጥብቆ የሚቃወመው። የትግራይ ህዝብን የኣምባገነኑ መደብ ኣጋር ኣድርጎ የሚያይ ሽባ ኣመለካክት ከሽባነቱ ኣልፎ የጋራ ትግሉን ኣደናቃፊ በመሆኑ ኣጥበቆ ይቃወመዋል። የኢህኣዴግ ገዥ ቱጃሮችን በማንበርከክ የሥልጣን ባለቤት ለመሆን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርገውን ትንቅንቅ ለመበረዝና የሚካሄደው ትግልን ተራ የብሔሮች ቅራኔ በማስመሰል እንዳንድ ቡድኖች ለፕሮፓጋንዳ፣ ለፖለቲካና ለንብረት ፍጆታ ሲሉ ትግሉን ጥላሸት ሊቀቡት የሚዳዱ ኣደናቃፊዎችም በጊዜ ሃይ ሊባሉ ይገባል።

በሌላ በኩልም ጥቅማቸው የተነካባቸው ወይም ከገዢው መደብ ጋር የተሳሰሩ የህወሓት ካድሬዎች ህዝቡ ከጭቆና ስለሚላቀቅበት መንገድ ከቁምነገር ሳይቆጥሩና ላንዳፍታም ቢሆን የህዝቡን መከራ ሳይመለከቱ፣ ህወሓት እንደ ድርጅት ስለሚሻሻልብት ዘዴ ሲመክሩ ይደመጣሉ። 'በሰብሰናል' ያለ ድርጅት ለመጠገን መሞከር ውጤቱ ኣብሮ መበስበስ እንደሆነ ልንነግራቸው እንወዳለን። የበሰበሰ ነገር ተወግዶ ለተኪው ኣዲስ ሁኔታ ስፍራው መልቀቅ ደግሞ ባህሪያዊ ነውና ከለውጥ ፈላጊው ሰፊው ህዝብ ጋር ቢራመዱ ለሁሉም ይበጃል። ከዚህም ይነሳ ከዛ ሁለቱም ጽንፈኛ ኣመለካከቶች ትግሉን የሚከፋፍሉ፣ ኣንድነታችንን የሚሸረሽሩ ለኢህኣዴግ ከፋፋይ ሴራ የሚያገለግሉ በመሆናችው ኣበክረን ልንቃወማቸው ይገባል።

የጎንደር ህዝብ ይሁን መላው ኢትዮጵያዊ የተነሳሳበትን የፍትህ፣ የኣንድነት፣ የሰላም ፍለጋ ትግል ማንም ሊያግደው የማይችል ማእበል ነውና፣ ጊዜ ሳይፈጅ ግቡ እንዲምታ በኣንድ ሃገራዊ ራእይ ስር ተሰባስበን እንታገል እንላለን።

የጋራ ጭቆና በጋራ ትግል ይወገዳል!!! የጋራ ሃገር በጋራ ጥረት ይለመልማል!!!
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት/ታንድ) ፣ 18-7-2016